የጎንደር ሕብረት

## ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ ቁጥር #6

## “ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ”

የጎንደር ህብረት ዛሬ ይህንን መግለጫ ለማዉጣት የተገደደዉ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ወደ ነባር የእናት ጎንደር አስተዳደር ለመመለሥ መብቱን ለማስከበር የጠየቀዉን ጥያቄ የወያኔ መንግስት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ እስከ አሁን ምላሽ ሳይሰጥ እሥራትና ግድያዉ እየባሰ መምጣቱ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ለዓለም ህዝብ ለማሳወቅ ሲሆን፤ እንዲሁም በሱዳን በኩል መሬት አሳልፎ የመስጠቱ ድብቅ ሤራ እስከ አሁኑ ሰዓት ቀጥሎ የትግራይ ታጣቂ ሚሊሻና የሱዳን ወታደሮችን ተመሳሳይ መለዮ ለብሰዉ በመተባበር በጎንደር ህዝብ ላይ ጦርነት መክፈታቸውን ለመላዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማስገንዘብ ነዉ።

የሁመራ፤ ወልቃይት ጠገዴ እና የጠለምት ህዝብ ሥብዕናዉን ተገፎ፤ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞበት፤ የሞተዉ ሙቶ የተረፈዉ ለስደት ተዳርጎ በባዕድ አገር እየታረደ፤ ሃገራዊ ዉርደት ደርሶብን በቁጭት ሃዘን ላይ አለን። አሁንም በአርማጭሆ፤ በመተማና በቋራ በኩል ከዉጭ ኃይል ጋር ተመሳጥሮ ቀስ በቀስ አራሽ ጎንደሬዉን ማፈናቀሉን አላቆመም። የወገኖቻችን ህይዎት በየቀኑ እየተቀጠፈ፤ ቤት ንብረታቸዉ እየወደመ ነዉ። ከዚህ ሁሉ ግፍ እና በደል የተረፋትን ወንድምና እህቶቻችን ወደባእድ አገር እንዲሄዱ የእርጎ ባህር በማሳዬት፤ በራሱ የደህንነት መስመር የኮንትሮባንድ ንግድ ከፍቶ እያጓጓዘ ገንዘብ የሚቸበችበዉ፤ የሚያሳርደዉ፤ ውቅያኖስ እና በረሃ እንዲበላቸው፤ በሳት እንዲቃጠሉ ምክንያት የሆነው እራሱ አሸባሪዉ ወያኔ ነዉ።

የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ብሎ እራሱን የሚጠራዉ ድርጅት፤ ሕዝባችንም፤ ኢትዮጵያ ሃገራችንም አጥፍቶ በዉጭ ዜጋ ለመተካት እዬተዘጋጀ ያለ የጥፋት መልክተኛ ድርጅት ነዉ። በተለይ ይህ አጥፊ ድርጅት ታላቋን ትግራይ ለመፍጠር የጎንደርን ታሪካዊ ቦታወች ወደትግራይ የማሸጋሸግ እና ለአጎራባች አገሮች ለም መሬታችን አሳልፎ የመስጠት አገር፤ ሕዝብ እና ታሪክ አጥፊ ሴራ በመጨህ ብቻ የሚያቆም አይደለም። ምርጫችን አንድ እና አንድ ነው። የወያኔን

ግፍ እና በደል ከመሸከም ይልቅ፤ ዛሬም እንደ ቀደሙት አባቶቻችን “እምቢ ለአገሬ፤ እምቢ ለነጻነቴ” በማለት ለራስ ነፃነት እና ለአገር ክብር አኩሪ መሥዋዕትነት ከፍሎ ለቀጣዩ ትውልድ ታሪክን ማውረስ ዛሬ፤ ወይም ነግ በሚል ቀን ቀጠሮ የማይሰጠው አንገብጋቢ ወቅት ነው። ይህ እንደሚሆን ደግሞ  መሰሪው ወያኔ መራሹ  መንግሥት ጠንቅቆ ያውቃል። በመሆኑም፤ አሥቀድሞ በተናጠል ወይም አንድ በአንድ፤ ትጥቅን በማሥፈታት፤ ነጥሎ ለመምታት ሙከራ እያደረገ ነው። አንተም ይህን የወያኔ መሰሪ ደባ ለመመከት ከተፈለገ፤ እንኳንስ መሳሪያህን፤ ቆመጥህን፤ ጭራሽ ልታሥነካ አይገባህም። ከዚህ ባሻገር፤ የጎንደርን ችግር ከደም መፋሰሥ በመለሥ ለመፍታት መሞከር አለበት ከተባለ፤ የመላዉ ጎንድር ህዝብ በሰባቱ አዉራጃወች ተጠራርቶ ጎንድር ከተማ ላይ ጉባዬ በመቀመጥ፤ የክልሉን መሪዎች አሥጨንቆ እና አሥጠብቦ፤ የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ ማስገደድ ከተቻለ መሞከሩ መልካም ነው። ይህም የአካባቢዉ አስተዳዳሪወች ትብብር ማድረግ እና የህዝብን ጭኸት ልብ ማለት የሚችሉ ከሆነ ነው። በርግጥም ለነሱም ቢሆን ሰላም የሚያመጣው ቀና መንገድ ይህ ብቻ ነዉና።

ሌላዉ ሳንጠቅስ የማናልፈዉ ጉዳይ ደግሞ በቅርቡ ከወልቃይት ጠገዴ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተከሰተዉ አሳዛኝ ነገር  ነዉ። ወደ ጎንደር ከተማ ለገቢያም ሆነ ለማህበራዊ ጉዳይ የተንቀሳቀሱ ወገኖቻችን ግርፋት፤ እስራት፤ ግድያ እና ንብረት ዘረፋ እየተካሄደባቸዉ እንደሆነ በየቀኑ ጭሆታቸዉን በማሰማት ላይ ናቸዉ።  የወልቃይት ጠገዴ የጠለምት እና የሁመራ ህዝብ የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባርን የቅኝ ግዛት ብሶቱን ለመግለጽ የመንግስት መሪን መጠየቅ ይቻላል፤ በሚል ተስፋ ባለፈዉ ወር ወልቃይት ጠገዴ ላይ ኃይለማሪያም ደሳለኝን ወያኔወች በጋበዙት ቦታ 8 ሺህ ህዝብ በሰልፍ ሲጠባበቅ የይስሙላዉ ክቡር  ጠቅላይ ሚኒስተር የወያኔን የትግል ዋሻ ጎብኝቶ ህዝቡን ሳያነጋግር ተደብቆ ፈረጠጠ። ይህ ድርጊት ከመነሻዉ ጀምሮ ጎንደርን የማዋረድ እና የመናቅ ወያኒያዊ በሽታ ነዉ። ይህ ነው “ባለቤቱን ካልናቁ፤ አጥሩን አይነቀንቁ” የሚያስብለው።

የጎንደር ህዝብ ቤተሰቡን ተንቀሳቅሶ እንዳይጠይቅ፤ በሩቅም በቅርብም ገቢያ እንዳይገበያይ፤ ወደ ጎንድር ከተማ ለሃዘንም ሆነ ለማህበራዊ  ወይም ለሃይማኖታዊ ጉዳይ ከቦታ ቦታ እንዳይንቀሳቀስ

በመታገዱ የህዝቡን የዕለት ኑሮዉን ተደጋግፎ እንዳይገፋ ለችግር ዳርጎታል። ነገሩ "በአባቱ ከተማ ልጅዬዉ ተቀማ" ሆነ።

ሌላዉ አስደንጋጩ ጉዳይ በጎንደር ህዝብ ላይ የሚያደርሰዉ በደል በመላዉ ኢትዮጵያ ቢከሰትም ጎንደርን ከሱዳን ጋር ሁኖ የመዉጋት ሴራ ግን በየትም አገር ታሪክ ያልተከሰተ ሃገራዊ ገመና ነዉ። እጅግ የሚገርመዉ ነገር ደግሞ፤ የጎንደርን ህዝብ ከተከዜ ምላሽ ድምበር የመንጠቅን ጥያቄ ለመመለስ እንደጠር የፈራዉ የወያኔ መንግስት ምረጡኝ ልምራችሁ ብሎ አይን አፍጥቶ በየ አምስት ዓመቱ መቅረቡ ደግሞ እጅግ ከመጠን ያለፈ ድፍረት ነዉ። ከጀርባ ግን፤ ሚሊሻ እያሰለጠነ የጎንደርን ባላባት ማፈን፤ መግደል፤ ትጥቅ ማስወረድ፤ የዉጭ አገር አራሾች ጋብዞ የጎንደርን መሬት ማስነጠቅ፤ አዝመራዉን ማቃጠል የሌተ ቀን ስራዉ ሁኗል።

የግፍ ቀንበር በዝቶባቸዉ ጫካ የገቡትን ወጣጥ ወንድሞች/ እህቶቻችን የድርጅት ስም እየለጠፈ በቤተሰብ ላይ የሚያደርሰዉ ሰቆቃ ፣ እስራት፤ ግርፋት እና ሃብት መዘረፉ የጎንድር ህዝብ ትግስቱ ተሟጠ መንግስት የሌለዉ መሆኑን አረጋግጧል። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ሁሉም በህብረት ተባብሮ እራሱን እና አገሩን የማዳን ታሪካዊ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት እንላለን።

ይህንን የጥቃት ዘመቻ ህዝቡ በሁለንታዊ ዘርፍ በአንድነት ተባብሮ መቋቋም የግድ ይላል። በጋራ ቁመን እራሣችን ካልጠበቀነ፤ ነጣጥለዉ፤ ከፋፍለዉ አንድ በአንድ እየቀፈቀፍ ወያኔዎች ይጨርሱናል። መሞታችን ካልቀረ፤ ለክብራችን እና ለነፃነታችን በጀግንነት እንሙት እንጂ፤ የወያኔዎች ግፈኛ ሞት ቤታችን እስከሚያንኳኳ መጠበቅም አይገባንም። አንዱ ሲታሰር ወይም ሲመታ ሁላችንም ተባብረን እንደ ንብ መዉረር አለብን። ነጻ የምነወጣዉ ይህ ከሆነ ብቻ ነዉ። ወንድሞቻችን፤ እህቶቻችን፤ አባት እናቶቻችን እየገበርን የቁም ሞት እጣ ተቀብለን በዉርደት እያለቀስን መኖር መቆም አለበት።

**የጎንደር/ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ**

የወያኔን የጭቆና አስተዳደር 24 ዓመታት በትግስት ብታሳልፍም፤ የአገር ድንበርን አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ በዋዛ የሚታለፍ ጊዜ  የሚሰጠዉ ነገር አይደለም። የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ለዘመናት ተከብሮ የኖረ መሬትህን ለራሱ ወደ ትግራይ ቆራርሶ እየወሰደ፤ በተጓዳኝ ደግሞ ለዉጭ ጠላት  የቋራን፤ የመተማን፤ የአርማጭሆን መሬት ከሱዳን ጋር መቃረጡን ቀጥሎበታል። ከአሁን ጀምሮ በአዉራጃ፤ በወረዳ እና በቀበሌ  ደረጃ ተመካክረህ ጎንደርን ካላስከበርክ ወያኔ ለም መሬት አልባ አስቀርቶ በተራራ አሽቀንጥሮ ሊጥልህ ቆርጦ ተነስቷል። ከእንግዲህ ይህን አዉቀህ ዉርደትን ላለመቀበል በብቃት ተዘጋጅ። ሌተ ከቀን ለፍተህ እና ደክመህ ያመረትከዉን የእርሻ አዝመራ የዉጭ ጠር  እያቃጠለ በጥይት፤ የሚያስደበድብህ እና የጠላትን የወረራ ዘመቻ የሚያስተባብረዉም ሆነ መንገድ መሪዉ ራሱ ወያኔ መሆኑን እዉቀሃል።

ከስምንት ዓመታት በፊት ለሱዳን በድብቅ ለማስረከብ የፈረመዉን መሬት እስከ አሁንም እየሸራረፈ ለመስጠት እያሤረ ያለዉ በጎንደር ላይ ታላቋን ትግራይን መፍጠር የሚል ዉዳቂ ዓላማዉን ለመተግበር ነዉ ። ይህን እቅዱን እዉን ለማድረግ ከዉጭ ጠላት ጋር ተባብሮብሃል። ጎንደርን በዉጭ ሃይል ለማስጠቃት የእጅ መንሻ ሰፊ እና ለም መሬት ሰጥቷል።

በቋራ ወረዳ፤ በማህበረ ስላሴ ከ30 ኪሎ ሜትር በላይ፤ ከደለሎ እስከ ጓንግ 40 ኪሎሜትር፤ ከደለሎ እስከ ሽመለ ጋራ የሁለት ሰዓት ጉዞ የሚፈጅ፤፤ በሁመራ በኩል ወደ ሱፍዋ 50 ኪሎ ሜትር፤ በአርማጭሆ በኩል እስከ 30 ኪሎሜትር፤ አብዛኛዉን የጎንደር ለም ቦታወች ከሱዳን ጋር ተስማምቶ ለመስጠት ፈርሟል። ተግባራዊ እንዲሆንም እያመቻቸ ነዉ። ይህ ጉደኛ ቡድን ያመጣዉን ገመና በሸፍኑ ለማስቀረት የመላዉ ጎንደር ህዝብ ማለትም የሰባቱ አዉራጃዎች ከጥቃት ለማዳን መመካከር አለባቸዉ። እረ ለመሆኑ ስንት ጀግና ያበቀሉ አዉራጃወቻችን፤ ተባብረው የጎንደርን መሬት ለማስከበር ያንሳሉ ወይ? ደባርቅ፤ ወገራ፣ ሊቦ፤ ድብረታቦር፤ ጋይንት፤ ጭልጋ እና ጎንደር ዙሪያ አዉራጃዎች ብቃት ያለዉ ጀግና ህዝብ ያፈሩ ናቸዉ። ይህ ሁሉ መሬት ሲወሰድ፤ አገር ጫታ አለመሆኑን መላዉ የጎንደር ህዝብ አዉቀታል? ዘረኛዉ መንግስት ያደረሰዉን የአስተዳደር ግፍ እስከ አሁን በትግስት አሳልፏል፤ በአገር ጉዳይ ግን ብዙ

ጭራሽ ቀልድ የለምና፤ ከእንግዲህ በቃ! ብሎ፤ ጎንደር  እራሱን ይጠብቃል። አቤት የሚልበት መንግስት ፍጹም የለዉምና።

የጎንደር ህብረት "ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ" ጥሪ ዋና ቁምነገር፤ ሁሉ ተባብሮ በህብረት ድንበሩን እና ነፃነቱን፤ ማስከበር የህልዉና ጉዳይ ነዉ የሚለዉን መልክት በጥብቅ ለማስተላለፍ ነዉ። ጎንደር ክፍለ ሀገር እያጣ ያለዉ ለም ቦታ ብቻ ሳይሆን፤ የቋራን የወርቅ ማዕድን ክምችት፤ የመተማን የነዳጅ ሃብት፤ ሌላም ከገመትነዉ በላይ የተፈጥሮ ጸጋችን ለመቆጣጠር ወያኔ እንደ እባብ በመሬታችን ዉስጥ ለዉስጥ እየተሳበ ነዉ። ጀግናዉ የአርማጭሆ ጠገዴ ህዝብ እስ አሁን ተከላክሏል፤ ተጋድሎዉን አሳይቷል። ከእንግዲህ ግን የመላዉ ጎንደር ህዝ አይዞን ሊለዉ ይገባል። መሃሉ ዳር እየሆነ ተራራ ላይ ኑሯችን እንዲሆን ወያኔወች እዬወሰኑልን ነዉና።

ከዛሬ 8 ዓመታት በፊት ከገዳሪፍ ክፍለ ሃገር ደንገል የሚባል የሱዳን ክፍለ ጦር ንፋስ ገቢያ የነበረዉን የኢትዮጵያዉያን የእርሻ ካምፕ አቃጥሎ፤ 2 ትራክተር እና 20 የእርሻ ካምፖች በእሳት ወደሙ፣ 27 አራሾች ካርቱም እስርቤት ታጎሩ፤ 3 ወደገዳሪፍ ተወሰዱ፤ አንድ ትራክተር ተወሰደ ። እንደሚታቀዉ  ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስተር መጀመሪያ ድርጊቱን ካደ። በሚቀጥለዉ ማለዳ ተገዶዶ መታሰራቸዉን እና ንብረታቸዉ መቃጠሉን አመነ። ዋሽቶ የማያመልጠዉ ነገር ግን በመሳሪያዉ ብቻ የሚመካዉ ወያኔ ዛሬም ማፈናቀሉን፤ በድብቅ መሬት መስጠቱን ቀጥሏል። ያኔ ጀግናዉ የወልቃይት ጠገዴ እና የአርማጭሆ ህዝባችን የሱዳንን አንድ አቶቡስ ሙሉ  ህዝብ ማርኮ የኛ ወንድሞችና እህቶች እንዲፈቱ አስገደደ፤ ተለቀዉም ወዳገራቸዉ ገቡ። ይህ በቅርብ ጊዜ ህዝባችን የፈጸመዉ መልካም ተጋድሎ እና አኩሪ ታሪክ ነዉ። አሁንም በየቀኑ ለዳር ድንበሩ ደሙን የሚያፈሰዉ በጠረፉ ያለዉ ብቸኛዉ የምዕራብ ጎንደር ህዝብ ነዉ።

በጎጃም በኩልም እስከ ጋምቤላ እጅግ ሰፊ መሬት  ለመስጠት ተፈርሟል። በትንሹ  ከ60 እስከ 80 ኪሎ ሜትር በወለጋ በኩል ወደዉስጥ የገባ ነዉ። አሁን ጉባ ተብሎ በሚጠራዉ በመተከል አዉራጃ የተጀመረዉ ግድብ ተጠናቆ ሃይቁ  ሲሞላ ከሱዳን ወደ 10 ኪሎ ሜትር ይቀርባል። ወያኔ የእንግሊዛዊውን የሻአለቃ ቻርለስ ጉዌንን የቅኝ ግዛት የወረራ ክልል በተቀበለዉ መሰረት

ግድቡ ዩሱዳን መሬት ላይ ሥላለ፤ የሱዳን ይሆናል ማለት ነው። ወያኔ ይህ ሃሰት ነው ካለ ለሱዳን አምኖ የሰጠዉን ካርታ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሳይ። ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ ቻርለስ ጉዌን በጉልበት የከለለዉን ካርታ አይቀበልም።

ቻርለሥ እራሱ በስልጣኑ ከንግስት ቢክቶሪያን መንግስት የኢትዮጵያን (POST) እንዳያልፍ የተሰጠዉን ምክር ሁሉ ቸላ ብሎ የኛን ድንበር በድፍረት ዘሎ  የኢትዮጵያን መሬት እንዳሰመረ በ67 እድሜዉ አካባቢ እያለ በ 1937 ዓ.ም በOXFORD JOURNAL ጋዜጣ ምስክርነቱን አብራርቶ ጽፏል። አጼ ሚኒሊክ መነሻ ያደረጉትን የቶማትን መስመር ትቶታል።  መከለሉን አገባዶ ወደ **እሙን ሃገር** እስከሚደርስና በመጨረሻ የአጼ ሚኒሊክ ስምምነት ወረቀት መጣ እስከሚባል ድረስ አብሮ ሲሰሩ የነበሩ የቀድሞ መሃዲስት ወታደሮችና ከግብጽ አገር የነበረ ዳንኤል ደስታ የተባለ የአማረኛ አስተርጓሚ የሽአለቃ ቻርለስ የቀጠረዉ ኢትዮጵያዊ አስተርጓሚ ብቻ  እንደነበሩ መስክሯል። ከዚያም ኢትዮጵያዊ ተወካዩች ተልከዉ እንደነበር ቢጠቅስም፣ ነገር ግን በህመም ምክንያት አብረዉ እንዳላካለሉ መስክሯል። በኬኒያም በኩል በተመሳሳይ መልኩ የእንግሊዝ ተወካዮች ብቻ እንዳሰመሩት አረጋግጧል።

አወ! ወያኔ የጎንደርን መሬት ነጥቆ ከትግራይ ህዝብ ጋር አቆራርጦ፤ ኢትዮጵያን በትኖ ለመጥፋት ወራሪ ያሰመረዉን ክልል አምኖ ሰጥቷል። ነገር ግን ይህ ሤራ ወያኔ  በመጨረሻ ለሞት የሚያደርሰዉ የተሸፈነ ገመናዉ እንድሆነ እርግጠኛ ነን። በድብቅ የፈረመዉን፣ ለጠላት  ቃል የገባዉን፤ በጋሃድ ማስረከብ ብቻ ሳይሆን፤ የጎንደር ህዝ ድንበሩን ሲጠብቅ ከኋላ በመዉጋት በዋናነት የሚገፋፋ መንገድ መሪዉም እራሱ ወያኔ መሆኑ እራሱን የቻለ አስገራሚና አስፈሪ በታሪክ የሚያሥጠይቅ ጉዳይ ነዉ።

## አሁንም! የጎንደር ህዝብ ሆይ!

በዚህ ወቅት ያጋጠመን አገር በቀል የጠላት ቡድን፤ ይቅርታን የማያውቅ፤ ትህትና የሌለዉ፤ መርዘኛ ድርጅት ነዉ። የእርሱ የሆኑ ካድሬወች ካንተ ጋር ለመስራት የሚፈልጉት አንተን

እየሰለሉ ለማጥፋት ካልሆን በቀር የመልካም ሥራ ግኑኙነት ፈጽሞ ሊኖራቸዉ አይችሉም። አንተን ቀርቶ የትግራይን ህዝብ የበሉ አዉሬዎች ናቸዉ እና። 24 ዓመታት ቸላ ስላልካቸዉ ከትዉልድ ቦታህ እያፈናቀሉህ በባዕድ አገር ሂደህ መታረድህ የሚያስደስታቸዉ ከኢትዮጵያዊ ወገንህ ሁሉ የተለዩ ከሃዲወች እንደሆኑ አዉቀህ ያለመጠራጠር ዳር ድንበርህን አንተዉ ተባብረህ አሥከብር። ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ወረዳ እና በአዉራጃ መላዉ ጎንደር ተመካክሮ፤ የቡድን መሪ መርጠ፤ አንዱ ሲታሰር/ስትታሰር ሁሉም አሻፈረን ብሎ ተባብሮ ማስፈታት ግድ የሚለን ወቅት ላይ ነን። ወያኔ ልጆቻችን ሲያሳድድ፣ የአርሶ አደሩ መሬቱ ሲነጠቅ፤ እያንዳንዱ ወጣት አዛዉንት እስር ቤት ተወርዉሮ ለስቃይ እዬተዳረገ፤ሌሎቻችን ዝም በማለታችን እንደ ፈሪ እና ተንበርካኪ እያስቀጠረን እንጂ ሰላም ፈላጊ መሆናችንን አይደለም እና ወቅቱ በቆራጥነት ክንዳችንን የምናሳይበት ጊዜ ነዉ።

ሌላዉ የጎንደር ህብረት አጥብቆ በቀጣይነት የሚያወግዘዉ፤ ጎንደርን በዘር የመከለል ማነቆ ድርጊት ነዉ። በሚቀጥለዉ ዓመት ለመከለል ተሰጠ የተባለዉ ጎንደርን በነገድ ክልል የመቀቀፍደድ አዋጅ ፍጹም ሊተገበር የማይችል ለጎንደር ህዝብ በተለይም ለዚህ ትዉልድ የማይበጅ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆናችንን ደጋግመን ባወጣናቸው የማዕድን መሬት ለመንጠቅ የታለመ እና አንዱን ነገድ በሌላዉ ላይ የማስነሳት የወያኔ አንቀጽ 39 ትዉልድና አገርን የሚገል፤ ቅድስት ኢትዮጵያን ያዋረደ የተጭናገፈ ስርዓት ሥልት ነዉ።

አሁንም በጥብቅ የምናሳስበዉና ወንድም ህቶቻችን የምንማፀነዉ፤ ይከለልን? ብለዉ የጠየቁ፤ እራሳቸዉን ተወካይነን ብለዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ግለሰቦች ታሪካዊ ማንነትን ወይም የነገድን ስም ከማስከበር አልፎ በመሬት መካለል እና ሕዝብን በጎራ መለዬት አስፈላጊ እንዳልሆነ አምነው እስከ አሁን የተፈጸመዉን ስተት አርመዉ የመላዉ ጎንደር ተወካይ መሆናቸዉን አስምረዉ፤ አቋማም ለመዉሰድ ህሊናቸዉን እንዲመረምሩና አብረን መክረን የጎንደርን ህዝብ በጋራ ማገዝ እንድንች ይተባበሩን ዘንድ ድጋሚ ጥሪያችን እናሥተላልፋለን።

**“ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ” ነውና የወያኔን የዱር አራዊት የአንቀጽ 39 የዘር ስርዓትን ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አልተቀበለውም። አንቀጽ 39 በጎንደር መሬት ላይ መከለልን ቀርቶ ከመዝገብ ማህደር ላይ ይፋቃል። ነገር ግን የነገዶች ማንነት ማለትም የቅማት ፤ የአማራ፤ የአገው፤ የሽናሻ፤ የቤተ እስራኤል ቋንቋ እና ማንነት ለዘመናት የነበረ በመሆኑ፤ አሁንም በጎንደሬ ኢትዮጵያዊነቱ በክብር ይቀጥላል። የጎንደር ብሎም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ ነውና። ሁሉም የጎንደር መሬት ግን የሁሉም ነው። ጋራና ሸንተረር አቋርጦ የሚያገናቸውን ታላቅ ምድር ማንም ደፍሮ ሊያካልል አይችልም፤ ከሆነም እርስ በእርሳችን ሊያጣሉን የመጣ ጠላት ዓላማ መሆን አለበት።**

**በመጨረሻ ማሳሰብ የምንፈልገው የጎንደር ሕብረት ያወጣቸው መግለጫወች ከዚህ ጋር ስድስት ናቸው። እስከ አሁን ለህዝብ የደረሱም ሆነ ወደፊት የሚወጡ መግለጫወች የድርጅቱ አርማ ሰባቱን አውራጃወች የሚወክል፤ ሰባት የብጫ ብርሃን ጨረር መስመሮች ያሉት እና የማለዳ ጎህ ሲፈነጥቅ የሚታይ የፀሐይ ብርሃን በአረንጓዴ ብጫና ቀይ ቀለም የተሸበበ፤ በማህጸረ ቃል ጎሕ የሚል ከክቡ ላይ ጽሁፍ ያለበት ነው። ከዚህ ሌላ በጎንደር ሕብረት ስም በራሪ ወረቀት በጎንደር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚሰራጭ ጽሁፍ የጎንደር ሕብርት ድርጅትን የሚወክል አለመሆኑን እናሳሥባለን።**

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

የጎንደር ሕብረት።

## gonderhibret72@gmail.com

www.gonderhibret.org

05/13/15